# የሚኪያ በህይሉ የቤተልሔም ት/ቤት የልጅነት አብሮ አደጎች የሀዘን መግላጫና የመፅናኛ መልዕክት

## ሚኪያ በህይሉን በሀዘን ላጣችሁ ሁሉ ፈጣሪ አምላክ መፅናናትን ይላክላችሁ!




በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሀዱ አምላክ አሜን! የእግዚያብሔር አብ ቸርነት፤ የድንግል ማሪያም አማላጅነት፤ የልጁ የእየሱስ ክርስቶስ ምህረት፤ የመንፈስ ቅዱስ ፀጋና በረከት፤ የጻድቃን ሰማዕታት ተራዳኢነት እህታችንን በሀዘን ከተነጠቅነው ቤተሰቦች፤ ዘመዶች፤ አብሮአደጎች፤ጎረቤቶች፤ ጓደኞችና የጥበቧ አፍቃሪዎች ጋር ሁሉ ይሁን አሜን! እሱ ሀያሉ አምላክ ልዑል እግዚያብሔር ብርታቱንና መፅናናቱን ለሁላችንም ይስጠን አሜን።

የኛ የሚኪያ አብሮ አደጎች ሀዘን ጥልቅና የመረረ ቢሆንም የውድ ቤተሰቦቿ፣ የቅርብ ዘመዶቿና የቦንቱ ናንሲ ሀዘን ግን ከእኛ በላይ የከበደ መሆኑን ከቅርብና ከሩቅ ሆነን በሚገባ ተረድተናል። በልጅነት ዕድሜ በቤተልሔም ት/ቤት ውስጥ አብረናት ያደግነው የእሷ ዘመን ተማሪዎች ከሀገር ውስጥም ሆነ ከባህር ማዶ ሁነን ውድ እህታችንን በሀዘን ስናስባት ሀዘናችሁ የእኛም ሀዘን መሆኑን በዚህ አጋጣሚ በመግለፅ ጭምር ነው። ሚኪያ ከእኛና ከብዙዎቻችው ዘንድ በአካል የተለየች ነገር ግን በውስጣችን ህያው ሁና የምትኖር የዘመናችን ዕንቁ ወጣት ነች። እግዚያብሔር መርጦ የሰጣትን የተፈጥሮ ችሎታ ያልቀበረች፤ ይልቁንም ለበጎ አላማ የተጠቀመችበትና ሀገርንና ህዝብንም በዓለም አቀፍ ደረጃ ለማስጠራት የሞከረች የሀገርና የህዝብ ወኪልም ነበረች። ብዙ ታአምር መስራት በምትችልበት የለጋነት ዕድሜ በአምላኳ ፈቃድ በመጠራቷ ድንጋጤውና ሀዘኑ ቅስማችንን ቢሰብረውም ትታልን በሄደችው ቅርስና ጥበብ ግን ወደፊት ስንዘክራት እንኖራለን። አብረናት ባደግንባቸው በእነዛ የማይተኩ የልጅነት ዘመናት ውስጥ ያጠራቀምናቸው ትዝታዎች እንዲህ በቀላሉ የሚዘነጉና ከአዕምሮአችን የሚጠፉ ባለመሆናቸው ምናልባት አንድ ቀን እሷንና ብዙዎቻችንን ያስተሳሰረውን የአብሮ አደጎች ትዝታ የምንተርክበት አጋጣሚ ወደፊት ይመጣ ይሆናል ብለን ተስፋ እናደርጋለን። ፈጣሪ አምላክ ነፍሷን ከአብርሃም ከያዕቆብና ከይስሐቅ ጐን ያሳርፍልን። ምህረትን ሰጦ ነፍሷን ይማርልን። እናንተን ውድ ቤተሰቦቿንም ብርታቱን፤ መፅናናቱንና ጥንካሬውን በቶሎ ይላክላችሁ እንላለን።

ከቤተልሔም ት/ቤት የልጅነት ጓደኞቿ

Yebethlehembach1990@yahoo.com

## ነፍስ ይማር

ከዚህ በታች ያለውን ግጥም ምትክ ለማናገኝላትና ገና በወጣትነት ዕድሜ ድንገት ለተለየችን **ገጣሚና ታዋቂ ድምጻዊ ሚካያ በህይሉ** ሳበረከት ከህጻንነት ዕድሜ ጀምሮ በቤተልሔም ት/ቤት ውስጥ አብረናት ባደግነው የእሷ ዘመን ተማሪዎች ስምና ከእኛ ዕድሜ በላይ እንዲሁም በታች በዛው ት/ቤት ውስጥ በተማሩ ተማሪዎች፤ መምህራኖችና ሰራተኞች ስም ጭምር ነው። የሚኪያ ድንገተኛ ህልፈት በተለይ ከሀገረ ኢትዮጵያ ተለይተው በምዕራቡና በተለያዩ ዓለም ሀገራት ለረጅም ዘመን የሚኖሩትን የቅርብ ቤተሰቦች፤ ዘመዶች፤ አብሮ አደጐችና የጥበቧ አፍቃሪዎች ከማስደንገጡም በላይ ለረጅም ዘመን በአካል ሳያገኟት በለጋነት ዕድሜ በመለየቷ የተሰማቸውን ከባድ የሀዘን ስሜት በአይነ-ህሊናዬ እንዳስተውለው አድርጐኛል። ህልፈቷን ድንገት በሰማሁበት ወቅትም የተሰማኝ ከፍተኛ የሀዘን ስሜት ከብዙዎቻችሁ ስሜት ጋር ይመሳሰል ይሆናል ብዬ ስለገመትኩ እንደ ፀበል ተረጭቶ የደረሰኝን በጣም ትንሽ የግጥም ስጦታ በመጠቀም የብዙዎቻችንን የሀዘን ስሜት (ከገለፀው በሚል) ከዚህ በታች እንደሚከተለው በግጥም ደረደርኩት ።

ከቅጥርዋ ግቢ ከሚሞቀው ጓዳ

ያቺ ቤተልሔም ኮከብ ወልዳ ወልዳ

እኔን ለምስክር እነሱን ለትንግርት ደባልቃ አሳድጋ

የማልከፍለውን ሞት እንደ ብድር አርጋ

በል ክፈል አለቺኝ ሚካዔን በዕዳ።
ምነው እትዬ ቆንጂት ምነው ጋሽ አዲሱ?
በተቀደሰው ቀን መርዶን ማርዳታችሁ በዕለተ ሐሙሱ።
ባሕር ማዶ ሆኜ ድምጿን ባየር ሞገድ ስጠብቅ በተስፋ

ቪኦኤ አረዳኝ ሳያስጠነቅቀኝ ገላልጦ በይፋ።
መርዶ ሞገድ ሆኖ ባሕር ተሻገረ
ደረት መቶ መቅበር ሳልስት መቀመጥ 40 ማውጣት ቀረ።
ያ የጥበቦች ቤት የምርጦች መፍጠሪያ
ቴድሮስን የሰጠን ሚኪያን የሰጠን ለሀገር ማስጠሪያ
ምን ብሎ ይሆን ይሆን? ድንገት ሞት ሲነጥቀው ኮከቡን ከጉያ?
አባቷ ወለዱ እናቷ ወለዱ ላገር የምትበቃ ኩሩ ኢትዮጵያዊ
ቅኔውን የምትዘርፍ፤ ወርቁን የምትመዝን፤ሰሙን የምታቀልጥ አማላይ ድምፃዊ
ግና ምን አተረፍን?
አስር ሀያ አመት አይኖችሽን ሳናይ አይናችንን ሳታይ ከአንጀት ተነፋፍቆ
በሬዲዮ ሞገድ ለዛውም በግላጭ መርዶሽን ጠብቆ
በባይተዋር አገር በባዕዳን ምድር በእንባ ተንሰቅስቆ
ሀዘን ያደማውን የልጅሽን አንጀት እንደ ዝናር ታጥቆ
ሰራቂ ድምፅሽን የጥንት ትዝታሽን ዘላለም ሰንቆ
ሚካዔን የሚያክል አብሮአደግ ያገር ልጅ በሀዘን ተነጥቆ
እ...ህ....እየተባለ በቁጭት ህይወት ላይ ፀፀትን አጥልቆ
ኪሳራ ነው እንጂ ትርፍማ መች ታውቆ!
እንግዲህ ቤተሎች እርማችሁን አውጡ
ድፍን ኢትዮጵያዎች እርማችሁን አውጡ
የድምጿ አፍቃሪዎች እርማችሁን አውጡ
አምላክ የጠራትን ምትክ ላታመጡ።
ከዚህ ከፉ ምድር የሱ-ዓለም ተሽሎ
የፈጠራት አምላክ ልውሰድሽ ነኝ ብሎ
በሰማዩ ገነት አኖራት ጨክኖ።
እንግዲህ ዘምሪ ከነኪሩቤል ጋር ከመላዕክቶች ጋር አውርጂ ምስጋና
ድሮም ስጦታሽ ነው ድምፅ ማንቆርቆሩ ማስረቅረቅ በዜማ።
እኛ ግን..........
ነፍስ ይማር፤.... ነፍስ ይማር፤..... ነፍስ ይማር...... ብለናል
ለእናትና አባቷ ለምትክ ልጇ፤ ለስጋዋ ከፋይ መፅናናት ልከናል።

ደረጀ ሙሉጌታ ተፈሪ ከአትላንታ

Yebethlehembach1990@yahoo.com